# ትምህርት 51

1. ኢየሱስ አይሁዶችን ማስተማር ሲጀምር ዕድሜው ስንት ነበር?

ሀ- 30 ዓመት።

2. ኢየሱስ ለሕዝቡ ያስተማረው የእግዚአብሔር ወንጌል ምን ነበር?

ሀ- የእግዚአብሔር ወንጌል የሰዎች ኃጢአት በሞት የሚቀጣ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ የሚያበስር ነበር።

3. እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲያድን የሚልከው አዳኝ ማን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ።

4. ኢየሱስ «ጊዜው ደርሷል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

ሀ- ኢየሱስ "አዳኙ የሚመጣበትና የእግዚአብሔር መንግሥት የሰይጣንን መንግሥት የሚያሸንፍበት ጊዜ ደርሷል" ማለቱ ነበር።

5. ሰው እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ ምንድን ነው?

ሀ- በእግዚአብሔር ቃል ማመን።

6. ኢየሱስ ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ የጠራቸው ለምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ የጠራቸው ሰዎች ሌሎችን ስለ እግዚአብሔር ማስተማር እንዲችሉ ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነበር።

7. የሕግ መምህራን እነማን ነበሩ?

ሀ- ፈሪሳውያን ነበሩ።

8. የኢየሱስ ትምህርት ከፈሪሳውያን ትምህርት የሚለየው በምን ነበር?

ሀ- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ፣ እግዚአብሔር አብን ያውቀዋል፤ ፈሪሳውያን ግን እግዚአብሔር አብን አያውቁትም።

ለ- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ያውቃል፣ ፈሪሳውያን ግን የእግዚአብሔርን ቃል አያውቁም።

ሐ- ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያምናል፣ ፈሪሳውያን ግን የእግዚአብሔርን ቃል አያምኑም።

9. በመጀመሪያ፣ አጋንንት ከመሆናቸው በፊት አጋንንት ምን ነበሩ?

ሀ- በመጀመርያ፥ አጋንንት ሰይጣንን ተከትለው ክፉ ከመሆናቸው በፊት፣ እግዚአብሔር መልካም አድርጎ የፈጠራቸው መላእክት ነበሩ።

10. አጋንንት፥ ኢየሱስ እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃሉ?

ሀ- አዎን።

11. አጋንንት ኢየሱስን የሚፈሩት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም አጋንንት፣ ኢየሱስ በፈለገው ጊዜ ወደ ዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ እንደሚጥላቸው ስለሚያውቁ ነው።

12. ኃጢአት ከለምጽ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ሀ- ለምጻሙ ራሱን ከለምጹ ማንጻት እንደማይችል ሁሉ፣ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ከኃጢአት ማንጻት አይችሉም።

ለ- ሌላ ሰው ለምጻሙን ከለምጹ ለማንጻት እንደማይችል ሁሉ፣ ማንም ሰው ከኃጢአታችን ሊያድነን አይችልም።

ሐ- ኢየሱስ ብቻ ለምጻሙን ከለምጹ ማንጻት እንደ ቻለ ሁሉ፣ ከኃጢአታችን ሊያድነን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።

- አንድ ሌሊት ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ኢየሱስን ሊጐበኘው መጣ።

## ዮሐንስ 3፥ 1-2

1- ከፈሪሳውያን ወገን ከአይሁድ አለቆች አንዱ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው ነበረ፤

2- በሌሊትም ወደ ኢየሱስ መጥቶ «ረቢ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ታምራዊ ምልክቶች ማንም ሊያደርግ ስለማይችል፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር እንደ ሆንህ እናውቃለን» አለው።

- አብዛኛዎቹ ፈሪሳውያን ኢየሱስን ይጠሉት ነበር።
- አብዛኛዎቹ ፈሪሳውያን ኢየሱስ ኃይል ያገኘው ከሰይጣን ነው ይላሉ።

- ኒቆዲሞስ ከእነርሱ የተለየ ሰው ነበር።
- ኒቆዲሞስ ኢየሱስን አይጠላውም ነበር።

- ኒቆዲሞስ ከኢየሱስ ጋር ለመነጋገርና ብዙ ጥያቄዎችን ሊጠይቀው ፈለገ።

- ኒቆዲሞስ ለኢየሱስ ምን አለ?

- ኒቆዲሞስ ኢየሱስን እግዚአብሔር እንደ ላከው እንደሚያውቅ ነገረው።
- ኒቆዲሞስ ኢየሱስን እግዚአብሔር እንደ ላከው በምን አወቀ?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚቻለውን ተአምራት ይሠራ ስለነበር።

- ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ምን መለሰለት?

## ዮሐንስ 3፥ 3

3- ኢየሱስም መልሶ «እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» አለው።

- ኢየሱስ “ማንም ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” አለው።

- ኢየሱስ ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ “ሰዎች ሁሉ የተወለዱት በሰይጣን ግዛት ውስጥ ስለሆነ፣ ዳግም መወለድ አለባቸው” ማለቱ ነበር።

- ሰዎች ሁሉ በሰይጣን ግዛት ውስጥ የተወለዱት እንዴት ነው?

- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተው ባመጹ ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር መንግሥት ተለዩ።

- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርተው ባመጹ ጊዜ፣ ከሰይጣን መንግሥት ሥር ሆኑ።

- የአዳምና የሔዋን ልጆች ቃየንና አቤል የተወለዱት በሰይጣን መንግሥት ውስጥ ነበር።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ሠርተው በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ፤ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን መንግሥት ውስጥ ተወለዱ።

- ኢየሱስ ሰዎች ሁሉ በሰይጣን መንግሥት ውስጥ ስለ ተወለዱ፣ ዳግም መወለድ አለባቸው ማለቱ ነበር።

- ኒቆዲሞስ ምን መልስ ሰጠው?

ዮሐንስ 3፥4

4- ኒቆዲሞስም «ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ እንዲወለድ ወደ እናቱ ማሕፀንስ ሊገባ ይችላልን?» አለው?

- ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ያለውን አልተረዳም።
- ኒቆዲሞስ ሰው እንዴት ዳግም እንደሚወለድ አላወቀም።

- ኒቆዲሞስ ኢየሱስ በሥጋ ዳግም ስለ መወለድ የሚናገር መሰለው።

- ኢየሱስ የተናገረው በሥጋ ዳግም ስለ መወለድ ነበር?
- አይደለም።

- ኢየሱስ ምን መለሰ?

ዮሐንስ 3፥5

5- ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ «እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።»

- ኢየሱስ ከውኃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ እንዳለብን ተናገረ።

- በመጀመርያ ኢየሱስ ከውኃ መወለድ እንዳለብን ተናገረ።

- ኢየሱስ «ከውኃ መወለድ» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- «ከውኃ መወለድ» ማለት «መጠመቅ» ማለት ነው?
- አይደለም።

- ኢየሱስ ዳግም ለመወለድ መጠመቅ ይገባናል ማለቱ ነው?
- አይደለም።

- ጥምቀት ሊያድነን ይችላል?
- አይችልም።

- ታዲያ ኢየሱስ «ከውኃ መወለድ» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ውኃ ቆሻሻውን ምን ያደርገዋል?
- ያነጻዋል።

- ውኃ ቆሻሻን እንደሚያነጻ ሁሉ ሰዎች ሁሉ ከኃጢአት መንጻት አለባቸው።

- ኢየሱስ ከውኃ መወለድ ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ከውኃ መወለድ ማለት እግዚአብሔር ከኃጢአታችን እንዲያነጻን ንስሐ መግባት ማለት ነው።

- ሁለተኛ ኢየሱስ ከመንፈስ መወለድ እንዳለብን ተናገረ።

- ኢየሱስ «ከመንፈስ መወለድ» አለባችሁ ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ሠርተው በእግዚአብሔር ላይ ባመጹ ጊዜ መንፈሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ሞቷል።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ሠርተው በእግዚአብሔር ላይ ባመጹ ጊዜ እግዚአብሔርን ለማወቅ፣ ለመውደድና ለመታዘዝ መንፈሳቸው ሞቷል።

- መንፈሳችን ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ስለ ሞተ እግዚአብሔር ለመንፈሳችን አዲስ ሕይወት መስጠት አለበት።

- ኢየሱስ "ከመንፈስ መወለድ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ከመንፈስ መወለድ ማለት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን አዲስ ሕይወት መስጠት ማለት ነው።

- ከውኃ መወለድ ማለት እግዚአብሔር ከኃጢአታችን እንዲያነጻን ንስሐ መግባት ማለት ነው።

- ከመንፈስ መወለድ ማለት መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን አዲስ ሕይወት መስጠት ማለት ነው።

- ኢየሱስ ኒቆዲሞስን "ዳግም መወለድ ያስፈልግሃል" ስላልኩህ አትገረም አለው።

ዮሐንስ 3፡7

7- ኢየሱስ እንዲህ አለው «ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ስላልሁ አትገረም።»

- ኒቆዲሞስ "ዳግመኛ መወለድ ያስፈልግሃል" ስለተባለ መገረም የሌለበት ለምንድን ነው?

- ኢየሱስ የተናገረው ይህን ነው፡

ዮሐንስ 3፡6

6- ኢየሱስ እንዲህ አለው «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው።»

- ኢየሱስ «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ ሥጋ መውለድ የሚችለው ሥጋን ብቻ ነው ማለቱ ነበር።

- ደግሞም ኢየሱስ ለሰው መንፈስ አዲስ ልደትን መስጠት የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው ማለቱ ነበር።

- እግዚአብሔር የሚለው በዚህ ዓለም ሁለት ዓይነት ሰዎች ብቻ እንዳሉ ነው።

- እነርሱም ነጭና ጥቁር ሕዝቦች አይደሉም።
- እነርሱም ሀብታምና ድኾች አይደሉም።
- እነርሱ ወጣቶችና ሽማግሌዎች አይደሉም።
- እነርሱ ወንዶችና ሴቶች አይደሉም።

- እግዚአብሔር በዓለም ላይ አሉ ያላቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን ናቸው?

- አንድ ጊዜ ብቻ የተወለዱና ዳግም የተወለዱ ናቸው።

- አንድ ጊዜ ብቻ የተወለዱት ሰዎች የማን ቤተሰብ አባላት ናቸው?

- የሰይጣን ቤተሰብ አባላት።

- ዳግም የተወለዱት ሰዎች የማን ቤተሰብ አባላት ናቸው?

- የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት።

- ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ሌላ ምን አለው?

ዮሐንስ 3፡14-15

14- ኢየሱስ እንዲህ አለው «ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ
ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤»
15- ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው
ነው። »

- የሙሴንና በምድረ በዳ የተሰቀለውን የናሱን እባብ ታሪክ ታስታውሳላችሁ?

- እስራኤላውያን ኃጢአት ስለ ሠሩና በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹ፣ እግዚአብሔር እንዲነድፏቸው መርዘኛ እባቦችን ሰደደባቸው።

- ብዙ እስራኤላውያን ከሞቱ በኋላ በሕይወት የነበሩት እስራኤላውያን ንስሐ ገቡ።

- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን የናስ እባብ ሠርቶ በእንጨት ላይ እንዲሰቅል ነገረው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን የተሰቀለውን እባብ ከተመለከቱ እንደሚፈውሳቸው ተናገረ።

- እስራኤላውያን ራሳቸውን ከሞት ማዳን ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- እስራኤላውያንን ከሞት ማዳን የቻለ ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር ብቻ።

- ኢየሱስና ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የናስ እባብ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

- ኢየሱስ ያለው እንዲህ ነው፡
- የናሱ እባብ በእንጨት ላይ እንደ ተሰቀለ፣ ኢየሱስም ይሰቀላል።

- እስራኤላውያን የናሱን እባብ ተመልክተው እንደ ዳኑ ሁሉ፣ ኢየሱስም በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ያድናቸዋል።

- ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ሌላ ምን አለው?

ዮሐንስ 3፡16

16- ኢየሱስ እንዲህ አለው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና።»

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለ ወደደ አዳኙን ኢየሱስን ላከ።

- በኢየሱስ ካመንን አንሞትም ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንኖራለን።

- ኢየሱስ ኒቆዲሞስን ሌላ ምን አለው?

ዮሐንስ 3፡17

17- ኢየሱስ እንዲህ አለው «እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው።»

- እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደዚህ ዓለም የላከው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ኢየሱስን የላከው በሰዎች እንዲፈርድ ነው?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር ኢየሱስን የላከው ሰዎችን ለማጥፋት ነው?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር ኢየሱስን ወደዚህ ዓለም የላከው ለምንድን ነው?

- ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል እንዲያድን ነው።
- ኢየሱስ ኒቆዲሞስን ሌላ ምን አለው?

ዮሐንስ 3፡18

18- ኢየሱስ እንዲህ አለው «በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል።»

- በኢየሱስ ባመኑት ላይ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል?
- አይፈርድባቸውም።

- በኢየሱስ ያላመኑት አሁኑኑ በእግዚአብሔር ተፈርዶባቸዋል?

- አዎን።

- በኢየሱስ ያላመኑት አሁኑኑ የተፈረደባቸው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር መሆኑን ስላላመኑ ነው።

- ኢየሱስ ኒቆዲሞስን ሌላ ምን አለው?

ዮሐንስ 3፡ 19-20

19- ኢየሱስ እንዲህ አለው «ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለ ነበረ፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤

20- ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤ አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም።»

- ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣው ብርሃን እርሱ መሆኑን ተናገረ።

- ኢየሱስ ክፉ ሰዎችን ብርሃኑን አይፈልጉትም አለ።
- ኢየሱስ ክፉ ሰዎች በጨለማ ውስጥ መሆን ይፈልጋሉ አለ።

- ክፉ ሰዎች በጨለማ ውስጥ መሆን የሚፈልጉት ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም ኃጢአታቸውን ስለሚወዱት ነው።

- ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መስማት የማይፈልጉት ለምንድን ነው?
- ኃጢአታቸውን ስለሚወዱት ነው።

- እናንተስ በጨለማ ውስጥ ከመሆንና የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት የቱን ትፈልጋላችሁ?